# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፣የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 14 ነሐሴ 15 2000 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ ! አባዝተው ያሰራጩ !

## የኑሮ ውድነቱ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶአል “የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዓለማቀፉን ህብረተሰብ ተስፋ አስቆርጧል” የአለም ባንክ

“በኢትዮጵያ የተከሰቱት ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዓለማቀፉን ህብረተሰብ ተስፋ እያስቆረጡት ነው” ሲል የዓለም ባንክ አስታወቀ።በዓለም ባንክ የኢትዮጵያና ሱዳን ዳይሬክተር ሚስተር ኪን አህሽ ሰሞኑን እንዳስታወቁት፤ ባለፈው ዓመት በተሰላው የሸማቾች መመዘኛ ዋጋ መሰረት በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ እየታየ ያለው አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት 55 በመቶ ደርሷል።በተለይ ረሀብና የምግብ እጦት ቀውስ፣የንግድ ሚዛን መዛባትና የውጭ ምንዛሬ መመናመን ዋነኞቹ ችግሮች መሆናቸውን ያመለከቱት ዳይሬክተሩ፤ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከውጪ አገር ዕቃ የማስገባት አቅማቸው ክፉኛ መዳከሙን ተናግረዋል።

“የዋጋ ግሽበቱ 55 በመቶ ደርሷል ማለት ምን ማለት ነው?” ተብለው የተጠየቁ አንድ ያኮኖሚ ባለሙያ፤”የአንድ ሰው የመግዛት አቅም በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር 55 በመቶ ወይም ከግማሽ በታች ቀንሷል ማለት ነው” ብለዋል።አቅም ባላቸው ያደጉ አገሮች ኢኮኖሚ ላይ፤ 10 በመቶ የዋጋ ግሽበት ሲታይ የሚፈጥረውን ድንጋጤና ተቃውሞ የሚያስታውሱ ወገኖች፤ እንደ ኢትዮጵያ ባለች ደሀ አገር 55 በመቶ የዋጋ ግሽበት ታየ ማለት ፤”አገሪቱ በደመ-ነፍስ ነው ያለችው” እንደሚያሰኝ ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የዓለም ባንክን አሀዝ በመቃወም የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ባወጣው መግለጫ፤”አጠቃላይ የዋጋ ግሽበቱ 55 በመቶ ሳይሆን 30 በመቶ ነው”በማለት ሊስተባበል የማይችለውን ዕውነታ ሊያስተባብል ሞክሯል።ወትሮ ከ500 ብር ብዙም ብልጫ ያልነበረው ኩንታል ጤፍ ዛሬ ወደ 1ሽህ 400 ብር፣ 200 ብር የነበረው ኩንታል በቆሎ ዛሬ ወደ 600 ብር፣ 300 ብር የነበረው ኩንታል ገብስ ዛሬ ወደ 700 ብር፣0. 80 ሳንቲም የነበረው ደረቅ እንጀራ ዛሬ ወደ 2ብር ከ 50 ሳንቲም፣ 0.50 ሳንቲም የነበረው የተጠበሰ እሸት በቆሎ ዛሬ ወደ 2 ብር ከ 50 ሳንቲም ወዘተ አሻቅቧል።ይህ ሀቅ በእህል ዋጋ ብቻ የታየው ጋሽበት ከእጥፍ በላይ መጨመሩን የሚያሳይ ቢሆንም፤ የስታስቲክስ ኤጀንሲ ግን በእህል ላይ የታየው የዋጋ ግሽበት 21 በመቶ ነው በማለት የችግሩ ገፈት ቀማሽ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ በዓለማቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ፈፅሞ ተዓማኒነት የሌለው አሀዝ አስቀምጧል።

ኤጀንሲው በመግለጫው፡-”የእህል ዋጋ መጨመር ለግሽበቱ ዋነኛ ምክንያት ነው” ካለ በሁዋላ ፡-”የእህል ዋጋ እንደ ታህሣስ ወር ቢሆን ኖሮ ግሽበቱ በዚህን ያህል ይቀንስ ነበር ” ማለቱ ብዙዎችን ፈገግ ከማሰኘቱም በላይ አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ፡-” ቢሆን ኖሮ ተብሎ ከተሰላ አይቀር ፤የእህል ዋጋ እንደ ሀይለሥላሴ ዘመን ቢሆን ኖሮ ተብሎ ግሽበቱ ቢሰላ ለኢህአዴግ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጥሩ አጋዥ መግለጫ ይሆን ነበር” ሲሉ ተሳልቀዋል።

## የጦር ወንጀሉ ተግባር ቀጥሏል “በሶማሊያ ወንድሞቻችን ላይ የሚፈፀመው ግፍ እኛን አይመለከትም” የኢትዮጵያ ህዝቦች

የኢትዮጵያ ወታደሮች ከበላዮቻቸው በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ባለፈው ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም ከሞቃዲሾ 18 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘውና ኤልሻብያ ተብላ በምትጠራው አካባቢ ሲጓዝ በነበረ የመንገደኞች አውቶቡስ ላይ በከፈቱት ተኩስ 65 ሲቪል ሰላማውያን የሶማሊያ ዜጎችን መግደላቸው ዓለማቀፉን ህብረተሰብ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብንም አስደንግጧል።

በድርጊቱ ከፍተኛ ሀዘን የተሰማቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ዝግጅት ክፍላችን በተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም የተሰማቸውን ጥልቅ ሀዘን ከመግለፃቸውም ባሻገር፤”በአቶ መለስ አገዛዝና መመሪያ በሶማሊያ ወንድሞቻችን ላይ እየተፈፀመ ያለው የማያባራ ግፍ፤እኛን የኢትዮጵያ ህዝቦችን አይመለከትም፤ ይህን ጭካኔ የተሞላበት አረመኔያዊ ድርጊት አጥብቀን እንቃወመዋለን”ብለዋል።

በርካታ ዓለማቀፍ ሚዲያዎች በሰላማውያን ዜጎች ላይ የተፈፀመውን አሰቃቂ ድርጊት ማጋለጣቸው ያስደነበረው የገዥው መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትናንት ባወጣው መግለጫ፤”የተባለውን ድርጊት አልፈፀምንም፤እኛ የገደልነው አሸባሪዎችን ነው፤ ታላላቅ ናቸው የሚባሉት ሚዲያዎች የውሸት ወሬ አናፋሾች ሆነዋል” በማለት ዛሬም ዘለፋውን ቀጥሏል።ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በ አዲስ አበባ የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ የአራተኛና የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ደጃፍ በጥይት በተገደሉ ምሽትና ማግስት የአገዛዙ ሹመኞችና መገናኛ ብዙሀን፤”የተገደሉት ባንክ ሊዘርፉ የሞከሩ ናቸው” በማለት ከ10 ዓመት የማይበልጡ ልጆችን “ባንክ ዘራፊ” አድርገው ማቅረባቸውን የሚያስታውሱ ወገኖች፤ዛሬም ሰላማውያንን ከገደሉ በሁዋላ “አሸባሪዎች”ማለታቸው ለዘር ማጥፋት ወንጀላቸው ሽፋን የሚያገኙ መስሏቸው ነው” ብለዋል።

**በሃገራችን ላይ የሚፈጸመውን የክህደት ወንጀል፣**
**በንብረታችን ላይ የሚፈጸመውን ዘረፋ፣**
**በመብታችን ላይ የሚጫነውን አፈና ለማስቆም፣በአንድነት እንነሳ።**
**አሻፈረኝ!በቃኝ!**
**ብለን የመለስ አገዛዝን እናስወግድ።**

# ርእሰ አንቀጽ

## በኦሎምፒክ ውድድሮች የሚወደሰው ነጻነት ነው::

ከክርስቶስ ልደት 500 አመታት በፊት ፤ፐርዢያኖች (ፋርሳውያን) አቴናን ለመውረር ከመምጣታቸው በፊት ከማዶ የምትታየዋን የኤርትራን ከተማ ወር ረው አወደሟት :: ወንዶቹን ጃንደረባ ፤ ሴቶቹንም ጋለሞታ አደረጓቸው :: ይህን ብከይ ከህድሞዎቻቸው ጣራ ላይ ሆነው የሚታዘቡት አቴናውያን ራሳቸው ባወጡት ህግ የሚዳኙ ፤ በመረጡአቸው እንደራሴዎች የሚተዳደሩ ዴሞክራቶች ነበሩ :: ህዝባዊ ስርአታቸውን በፍርሃት ተንበርክከው አሳለፊው ለባርነት ከመዳረግ የፋርስን ንጉስ ዳርዮስን ለመግጠም ወሰኑ :: የፐርዥያን 1/3ኛ የሚሆን የሰለጠነ ወታደር ሳይሆን ፤ ሃገር ወዳድ የዜጎች ጦር አሰልፈው የአማልክታቸው የዜዮስ ቤተመቅደስ ከሚገኝበት ተራራ ሥር ይጠባበቁ ጀመር :: መስከረም 11 ቀን 490 ዓመተ አለም ጦርነቱ ሲጀመርም ፤ ያ በፈረሰኞቹ ብዛት ፤ በመርከበኞቹ ቁጥር ይተማመን የነበረ የፋርስ ጦር በአቴና የህዝብ ሠራዊት ድባቅ ተመታ :: 6400 የፋርስ ወታደሮች ተገደሉ :: የተረፉት በመርከብ ተጭነው ሸሹ :: ድሉንም ለማብሰር ፊዲፒዲስ የተባለው የአቴና ጦረኛ ከጦሩ አውድማ ከሆነው ከማራቶን እስከ አቴና ድረስ 40 ኪሎ ሜትር ሮጦ «ደስ ይበላችሁ ድሉ የኛ ሆነ!» ብሎ ተንፍሶ ልቡ ፈንድቶ መስዋዕት ሆነ :: ይህንን ድል ለማብሰር ያደረገው የማራቶን ሩጫ ነው ኦሎምፒክ እየተባለ በየአራት አመቱ ሲከበር የሚኖረው :: ፖለቲከዊ ነፃነት የሚለው ቃል በራሳቸው ስምምነት ያቆሙትን መንግስት ለመከላከል የአቴና ዴሞክራቶች ያሳዩትን ቆራጥነት ተምሳሌት ያደረገ ሆኖ ፅንሰ-ሃሳቡ የተ ወለደው ከዚህ ዘመን በሁዋላ ነው :: አንድ ነፃ ህዝብ ለጥጋበኞች (ሂዩብሪስ) የማይገዛ ብቻ ሳይሆን፤ ምን ደካማ ቢሆን፤ ውሎ አድሮ የሚረታቸው መሆኑንም ለማብሰር የተፀነሰ ሃሳብ መሆኑ ነው :: **አንድ ነፃ ህዝብ በፍላጎቱ ያቆመውን ብሄራዊ መንግስትና አስተዳደር ለእብሪተኞች አሳልፎ እንደማይሰጥና ፤ ምን ደካማ ቢሆን መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ከፍሎ ፤ ነፃነቱን መቀዳጀቱ የማይቀር መሆኑን ለማስረገጥም ጭምር ነው የማራቶንና ኦሎምፒክ ምንነትና አንድምታ::**

የ18ኛው ክፍለ ዘመን የብሪታኒያ ፈላስፋና የታሪክ ተመራማሪ የሆነው ጄምስ ሚል «ለእንግሊዝ ነፃነት ከሄስቲንግስ ውጊያ ይልቅ ማራቶን የበለጠውን አስተ ዋፅኦ አድርጎአል» ማለቱም ፤ በዴሞክራሲ መኖር ካልቻሉ ለመሞት የቆ ረጡት አቴናውያን ያሳዩት ቆራጥነትና የተቀዳጁት ድል ይበልጥ ለነፃነት እንድንነሳሳ አስተምሮናል ማለቱ ነበር :: አስተውሎ ላጤነው ይህን የመሠለ ተምሳሌት ያቀፈ ነው የማራቶንና የኦሎምፒክ ትርጉም :: ምክንያቱም ሰው በባህሪው የሚገሰግሰው ወደበለጠ ነፃነት ፤ ወደፈጣሪው ልዕ ልና በመሆኑ፤ እንድ ሰው ፍጡር አንድ የሚያደርገውን ሃሳብ ለማክበር ነው በአራት አመታት አንዴ እየተገናኘ እርስ-በርሱ በመወዳደር ወደላቀና ይበልጥ ወደሰመረ ወደአርያም በአካሉም፤ በአእምሮውም፤ በመንፈሱም ለመመንጠቅ የሚታገለውና የሚያሻቅበውም ::

የኦሎምፒክስ ዋናው ማጣጣሚያ ውድድር ሌላ ሳይሆን የማራቶን ሩጫ የሆነውም ፤ ይሄንኑ 2500 አመታት ታሪክ ያስቆጠረውን የነፃነት ማብሰር ሩጫ የሰው ልጅ የሚጋራው ህልም በመሆኑ ነው :: ባለፉት 50 አመታትም የዚሁ የማራቶን ቁንጮ ሌላ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን የሚናኙበት መስክ መሆኑ የነፃነት ጥማታችን እያቅበዘበዘን የምናገኘው ድል በመሆኑ ነው ማለት ሃቁን መረዳት ይመስለናል :: ትንሽ አይደለንም ፤ ረሃብተኛ አይደለንም ፤ ባለታሪክ ባለቅኔ፤ ባለባህል ባለወኔ ትልቅ ህዝብ ነን ለማለት ይመስለናል ሯጮቻችንን ሃይ ሃይ እያለ ከሁዋላ የሚገፋቸው ሃይል :: አልሞትንም ለማለት ፤ ገና ወጋህታ ነው ለማለት ፤ የነፃነት ጎህ ጭላንጭሉን እንጂ ገና ብርሃኑን አላየንም ለማለት ይመስለናል በአያቶቻቸው ወኔ 40ውን ኪሎሜትር በሁለት ሰአት ውስጥ የሚያጣጥሙት :: እነዚህ የማራቶን ጀግኖቻችን በግላቸው አምጠው የወለዱትን ክህሎት ነው እንደ ህዝብ በጋራ መገላገል አቅቶን የኖረነው :: ግንቦት 7ንም በኢትዮጵያችን ታሪክ ልዩ የሚያደርገው ፤ የማራቶን አትሌቶቻችን ባለፉት ሃምሳ አመታት በግል ያነቁትን ሃቅ ፤ እንደ ሃገርና እንደ ህዝብ የጨበጥንበት ቅፅበት በመሆኑም ጭምር ነው :: እንደ ንቅናቄም አናስነጥቅም የምንለው ይህን የዴሞክራሲ ነፃነት ዕውነት ነው :: ህዝባችን ፈግጦ ፤ ተዋርዶ ፤ ተንቆ ፤ ተርቦ ፤ ተጠምቶ የደረሰበት ቅፅበት በመሆኑ ፤ ከዚህ ከደረሰበት ከፍታ ላነሰ ሽርፍራፊ አንደራደርም ነው የምንለው :: የሰው ልጆች የጋራ ርዕይ ከሆነው ዴሞክራቲክ ነፃነት ህዝባችን እንዲቋደስ የምንታገል በመሆኑም ፤ በዚህ የኦሎምፒክ ሳምንት ለአትሌቶቻችን የማራቶን ወርቃማ ድልን፤ ለህዝባችን ደግሞ የግንቦት ሰባት ማራቶናዊ ህልሙን ዕውንነት እንመኛለን ::

## የአሜሪካ ኤምባሲ በርእሰ አንቀጹ ላይ ማስተካከያ እንዲደረግ ጠየቀ

የግንቦት 7 ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ልሣን፣"የአሜሪካ ኤምባሲ ዳግም ሢሳሳት" በሚል ርዕስ በሃምሌ 10 ቀን ባወጣው ርዕሰ-አንቀፅ ላይ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ማስተካከያ እንዲደረግ ጠየቀ። ይህ የተገለጸው ከኤምባሲው በኢሜል በደረሰን ደብዳቤ ነው፡፡ ኤምባሲው በዚሁ ደብዳቤው ሃምሌ 17 2008 ዓ.ም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ባወጣቹሁት በግንቦት7 ልሳን ርእሰ አንቀጽ "'ምርጫ ቦርድ ገለልተኛ ተቋም ነው ብላችሁ ተቀበሉ፣ በመጪው ምርጫ እንደምትሳተፉ አረጋግጡ'፣ በማለት አምባሳደር ያማሞቶ እንደተናገሩት ተደርጎ የተቀመጠው በትክክል በአምባሳደሩ አንደበት የተነገረ ባለ መሆኑ ልሳኑ ማስተካከያ እንዲያደርግ እንጠይቃለን" ብሏል፡፡ የግንቦት7 ድምጽ ዝግጅት ክፍል ይህን ደብዳቤ መነሻ በማድረግ የኤምባሲውን የስራ ሃላፊዎች ያነጋገረ ሲሆን ኤምባሲውን በመወከል አንድ ዲፕሎማት ደብዳቤውን ለመጻፍ ያነሳሳን "መረጃውን ያገኛችሁት ከሌላ ሰው ሆኖ ሳለ አቀራረባችሁ ግን እራሳችሁ በቀጥታ ከአምባሳደሩ እንደሰማችሁት አድርጋችሁ ማቅረባችሁ ነው"ብለዋል፡፡በዚህ የስልክ ውይይት ላይ በተነሳው ጭብጥ ዙሪያ የ ኤምባሲውን አቋም ማወቅ እንደምንፈልግ ላቀረብነው ጥያቄ ኤምባሲው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኑን እኚሁ ዲፕሎማት ከማስታወቃቸውም ባሻገር ለቃለ ምልልስ በቀጠሮ ተለያይተናል። በእዚህ መሰረት የግንቦት 7 ድምጽ በሃምሌ 10 2000 ዓ.ም ባወጣው ርእስ አንቀጽ የመጀመሪያው መስመር ላይ ‹ሰሞኑን የአሜሪካን አምባሳደርና ባልደረቦቻቸው› በማለት ከሚጀምረው አረፍተ ነገር በፊት ......› **ዜና አቀባዮቻችን እንደጠቆሙን** የሚል ስንኝ ጨምረው አንባቢዎቻችንን አስተካክለው እንዲያነቡት በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

## የጥበብ አንቀጽ

### አንድ ነገር ብቻ ጎደለ

ዛሬም ኦሎምፒክ አማረ-
በወርቅ በብር ከበረ፣
እጅ መንሻውን ያው ሰጠን-
ዓለም የልምዱን ገበረ፣
በሰፊው ቤጅንግ ሜዳ ላይ-
አረንጓዴው ጎርፍ ተመመ፣
ኸልቅያው ሁሉ ፈዘዘ-
በኒ አደሙ ደመመ፣
ምስጋና ይሁን ለጀግኖች-
ዛሬም የልምዱ ድል አለ፣
በአዲስ ዝማሬ ለመጮኸ-
ልባችን ተቀጣጠለ፣
**ከየት እናምጣው ዜማውን-**
**ቴዲ አፍሮ ካ'ገር ከሌለ?**
**ልክ እንደ ያኔው አሁንም-**
**ግብሩ ተገኝቷል ሁሉ አለ፣**
**የቴዲ ብቻ መወድስ-**
**መረዋ ዜማ ጎደለ።**

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## ከሙሻራፍ ካልተማሩ፣ ከቻውቼስኮ ይማራሉ !!

ከአገሬ ከወጣሁ አንድ አመት ያለፈ መሰለኝ።አገር እጅግ ይናፍቃል።አንዳንዴ ጓደኞቼን አገሬ ናፈቀችኝ ስላቸው፣ “ምንነካህ ያች አገር! ምኗ ይናፈቃል፤አሁን ያለህበትን ነጻነት አስብ፣የምትኖርበትን ምቾት ተመልከት፣ ኢትዮጵያ ብትሆን እንዲህ ትኖራለህ? እንጀራ ነውችግርህ? እርሱም ሞልቷል፣የጤፍ ባይሆን የስንዴ አለልህ፣ እንኳን አንተ እዚህ ያለህው የኢትዮጵያ ህዝብስ ጤፍ መብላት ካቆመ ወራት ተቆጥረው የለም ወይ?” ይሉኛል። እዚህ በምኖርበት ሃገር አንድ ጊዜ አንድ የትምህርት ቤት ዳይሬክተር የኔንና የጓደኛን ታሪክ ሰምቶ፣ለተማሪዎች ታሪካችንን እንድንናገር ወደ ትምህርት ቤቱ ጋበዘን። የኔዘርላንድስ ልጆች ገና ሳይወለዱ መብታቸው ተከብሮ ስለሚያገኙት፣ ስለመብት ሲነግሯቸው አይገባቸውም፣ “መንግስት” መብት ሰጪና ነፋጊ መሆኑን አያውቁም። መንግስት መኖሩም እስከነጭራሹ ትዝ አይላቸውም።ታዲያ እኛን የጋበዙን፣ የኛን አገር ሁኔታ በመናገር ልጆቹ እንዲህ አይነት አለምም አለ እንዴ? ብለው የራሳቸውን እንዲያደንቁ ነበር። በዚህ መሀል ምን እንደምናቀርብ ከጓደኛዬ ጋር ተነጋገረን። በተቻለን ሁሉ ጥሩ ነገር ለመናገር ቃል ገባን። ስለኢትዮጵያ ውበትና ባህል ተናግረን ስንጨርስ ስለፖለቲካው ማንሳት ግድ ሆነብን። ከዚህ በሁዋላ ወጣቶቹ ጥያቄ መጠየቅ ጀመሩ። እኛም ግራ መጋባት ጀመርን። ለምሳሌ “ነጻ ፕሬስ ምንድነው?” ረሃብስ? ይሉሀል። እነርሱ ጋ ፕሬስ ነጻናነጻ ያልሆነ የሚባል ነገር የለውም። ረሃብንም ቢሆን በታሪክና በቴሌቪዥን መስኮት እንጂ በተግባር ምን እንደሚመስል አይረዱትም፣በመተርጎም ይረዳን የነበረው አስተማሪ ሳይቀር ልጆቹን ለማስረዳት ግራ ገብቶት ተቸገረ።

የሃገሬን ጉዳይ ስለምከታተል ኢንተርኔት ዜና እከታተላለው ይህም ሆኖ አንድም ቀን ደስ የሚል ወሬ ሰምቼ አላውቅም። ዘወትር “ሶማሌያ ውስጥ ወታደሮች ሞቱ፣ ህዝቡ በረሀብ አለቀ፣ የኑሮ ውድነቱ ሰማይ ደረሰ” ከሚል ዜና ጋር ነው የምፋጠጠው።

በተለይ ኑሮ ውድነቱ እንደዘንድሮው የከፋበት ጊዜ በታሪክ ታይቶ ስለ መታወቁ እጠራጠራለሁ። ክፉ ቀን እየተባለ ከሚጠቀሰውና በምኒልክ ጊዜ ከታየው ረሀብ ጋር ሲነጻጸር እንደ አሁኑ ጊዜ ያለ ችግር ያጋጠመን አይመስለኝም። በዚያን ጊዜስ እርደታ ከውጭ አይገባም ነበር፣ ዛሬ ግን እርዳታው በገንዘብና በእህል እንደ ዝናብ እየወረደ እንኳን ገበያው ሊጠግብ አልቻለም። በእውነቱ እጅግ ያስፈራል። ያስፈራል ብቻ ሳይሆን ያሸማቅቃልም። የኢትዮጵያ ህዝብ በውጭ አገር ስለረሀቡ የሚባለውን ነገር ቢሰማ እርዳታ መቀበሉን ትቶ በረሀብ ማለቁን ይመርጥ ነበር። ፈረንጆቹ በጣም ነው የሚያዝኑብን፣የነመለስ ሬድዮና ጋዜጣ እውነቱን ስለሚደብቁ ነው እንጅ የአለም ህዝብ የኢትዮጵያን ረሀብ ከስንፍና ጋር እያያዘው፣ ይንቀን ጀምሯል። እውነቱ ስንፍና አለመሆኑን መንገር ደግሞ የኛ ድርሻ ይመስለኛል።

የመለስ ሬዲዮና ጋዜጦች የኑሮ ውድነቱን ከአለማቀፍ የኑሮ ውድነት ጋር እያያያዙ የኢትዮጵያን ህዝብ ለመደልል ሲሞክሩ ይታያሉ። አንድ ሰሞን በእንግሊዝ የታየውን የዋጋ ንረት አጉልተው በማሳየት፣ ከተጠያቂነት ማምለጫ ሰበብ ለማድረግ እየሞከሩ ነው ። በአለማቀፍ ደረጃ የዋጋ መናር መታየቱ እውነት ቢሆንም፣ ኢትዮጵያን አሁን የገጠማት ችግር ምናልባት ከዝምባብዌ ይሻል እንደሆነ እንጅ ከየትኛውም አለም ጋር የሚወዳደር አይደለም። ለምሳሌ በጎረቤት ኬንያ ምግብ ተወድዶ ነበር፣አሁን ግን ወደ ነበረበት ቦታ ተመልሷል። እንዲያውም አሁን የእርዳታ ድርጅቶች ከአፍሪካ አገሮች እህል ሸምተው ወደ ኢትዮጵያ ሊልኩ መሆኑን አንብበናል። ግን እነመለስ ለጥፋታቸው ማምለጫ የእንግሊዚን ችግር እያወሩ ነው።

የኑሮ ውድነት ጎበኛቸው ከሚባሉት የአውሮፓ አገሮች መካከል እኔ የምኖርባትን ኔዘርላንድን ሁኔታ እንመልከት። በዚች አሩሲን በማታክል አገር የምግብ ዋጋ ጣራ ቢነካ፣ ህዝቦቿን በቀን ለፈለጉት ያክል ጊዜ ከመብላት የሚያግዳቸው ነገር የለም። በምእራብ አውሮፓ አገሮች የምግብ ዋጋ መጨመር፣ አገሮቹን ወደ ረሀብ የሚለውጥበት ሁኔታ የለም። የሰው ልጅ በምግብ እጥረት ሲቸገር የሚመለከቱት፣ ከቴሌቪዥን ላይ ነው። የእነርሱ ችግር የሚበላ መጥፋቱ ሳይሆን፣ ብዙ እየበሉ መወፈራቸው ነው። እንኳንስ እነርሱ ውሾቻቸው፣ የራሳቸው የሆነ ከገበያ የሚሸመት የተዘጋጀ ቀለብ በየሱፐር ማርኬቱ መደርደሪያ ከጎደለ ጉድ ፈላባቸው፣ለቤት እንስሳቱ የሚገዛላቻው ምግብ ባዶ አጥንት ሳይሆን፣ በውስጡ የያዘው ንጥረነገር በባለሙያዎች እየታየ ነው። ውሾችም እንደሰዎች እንዳይወፍሩ ክትትል ይደረግላቸዋል።ለውሾች ህክምና የሚወጣው ወጪ በእኛ አገር አንድ ሀብታም ለህክምና ከሚያወጣው አይተናነስም። የእኔ ጎረቤት ሁለት እባቦች አሉት።ለእባቦቹ የሚያወጣላቸው ወጪ እጅግ ብዙ ነው። የአንድ ጊዜ ቀለባቸውን ለመሸፈን በኢትዮጵያ እስከ 100 ብር ያወጣል። ልብ በሉ፣ እነመለስና አጋፋሪዎቻቸው የኢትዮጵያን የኑሮ ውድነት፣እንዲህ የተቀማጠለ ኑሮ ከሚኖረው የአውሮፓ ህዝብ ጋር ነው ለማወዳደርና ህዝቡን ለማሳመን የሚሞክሩት። በየትኛው አመክንዮ ነው ለውሻው የተመጣጠነ ምግብ በሚያበላና የሚበላው ባጣ ህዝብ መካከል ንጽጽር የሚደረገው?በዚህም ተባለ በዚያ፣ የኢትዮጵያ ችግር የአስተዳደር መበላሸት ያመጣው ችግር ለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም።

ተፈጥሮ ጎድቶናል፣ አይካድም።ታሪካዊ ችግሮች ነበሩብን፣ አይካድም። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ችግሮች የተስተካከለ ስርአት ቢኖረን ኖሮ ለመቀረፍ አስቸጋሪ አይደሉም፣ ሌላው አለም ከዚህ የተለየ ታሪክ አልነበረውም። የአስተዳደር መበላሸቱ በነጻነት እንዳንወስን፣ በነጻነት እንዳናስብ፣ በነጻነት እንዳንሰራ፣የሰራነውን በነጻነትና በፍትሀዊ መንገድ እንዳንከፋፈል አድርጎናል።ከእርዳታ ድርጅቶች የምናገኘውን ገንዘብ እንኳ በተገቢው መንገድ እንዳንጠቀምበት አድርጎናል። አሁን በአገራችን እየታየ ያለውን ቀውስ የምንፈታው በዋናነት አስተዳደሩን በመቀየር ይመስለኛል። አሁን ያለው አስተዳደር ከ17 አመታት የስልጣን ጊዜ በሁዋላ፣በመጨረሻ የተወልን ብዙ ሚሊዮን የተራቡና የተቸገሩ ወገኖችን ነው። በሁሉም መስክ፣ በሁሉም መመዘኛዎች ስርአቱ ፈተናውን ወድቋል። በእኔ በኩል ሁለት መፍትሄዎች ይታዩኛል፦

አንደኛ፣መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ፣ በብቃት ማነስ ምክንያት አገሪቱን አደጋ ውስጥ እንደጣሏት ተረድተው የፓኪስታኑ ፕሬዝዳንት ፔርቬዝ ሙሻራፍ እንዳደረጉት ስልጣናቸውን በገዛ ፍቃዳቸው መልቀቅ ነው።ይህን ካደረጉ አገሪቱን ከከፋ ምስቅልቅል በጊዜ መታደግ ይቻላል ። ይህን ካደረጉ በፈለጉት አገር በሰላም መኖር ይችላሉ። እስከዛሬ ለፈጸሙት ወንጀልም ይቅር እንላቸዋለን። ይህን ካላደረጉ ግን ሁለተኛው መንገድ ፣ የሮማኒያው ቻውቼስኮ እጣ ፈንታ ይከተላቸዋል።ህዝቡ ረሀቡንና የኑሮውድነቱን መሸከም ሲያቅተው ሆ ብሎ መነሳቱ አይቀሬ ነው። አሁን11ኛው ሰአት ላይ የምንገኝ ይመስለኛል። የሚቀረው እሳቱን ማፈም ነው። በግንቦት የተነሳው እሳት ተዳፈነ እንጅ አልጠፋም። እሳቱን ማቀጣጠልና እነመለስ ዜናዊ እንዲሞቁት ማድረግ ለነገ የማይተወው ስራ ነው። ህዝቡ ሲሞት እያየን እጃችንን አጣጥፈን ከተቀመጥን እኛም፣ ሳናውቀው የነመለስ አካል ሆንን ማለት ነው።

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## ከእዚህ ጭካኔ ለመገላገል ምን...? ? ?

ጋቹዬ

ሁለተኛው "የኢህአዴግ ፓርላማ" ሲከፈት አንድ የፓርላማ አባል ፦"ክቡር ፕሬዚዳንት፣ ባለፈው ክረምት በተካሄደው ምርጫ በደቡብ ክልል ዕጩ አድርገን ያቀረብናቸው ሰምንት አባሎቻችን በኢህአዴግ ታጣቂዎች ስለተገደሉብን፤ ይህ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት መስዋዕት ለሆኑት አባሎቻችን የህሊና ፀሎት እንዲደረግልን እጠይቃለሁ"በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ፤በወቅቱ ፕሬዚዳንት በክቡር ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ተቀባይነት በማግኘቱ፤የህሊና ፀሎቱ እንዲደረግ ፓርላማውን ጠየቁ። ፀሎቱ ተደረገ። ልክ የፓርላማ አባላቱ የህሊና ፀሎቱን ጨርሰው መቀመጫቸውን እንደያዙ ሰውየው እሣት ጎርሰው፣እሣት ልሰው ተነሱ-አቶ መለስ።

እጃቸውን በማወናጨፍና ዓይናቸውን ፕሬዚዳንቱ ላይ በማፍጠጥም በሀይለ-ቃል እንደሚከተለው ተናገሩ፦" አሁን የተደረገው ነገር ፈፅሞ ስህተት ነው፤ ለዚህ ምክር ቤትና ለፓርላሜንታዊ ስርዓት የበቃነው በእልፍ ታጋዮች ደም እንጅ በዘጠኝ ሰዎች መስዋዕትነት አይደለም።ስለዚህ የህሊና ፀሎት ለዘጠኝ ሰዎች መደረጉ ስህተት ነው"

ልብ በሉ፣ እዚህ ላይ፦"ለታጋዮቹም፣ ለዘጠኙም ሰዎች በአንድ ላይ ፀሎት ይደረግ" አለበለዚያም ፦"ለዘጠኙ ሰዎች እንደተደረገ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ ለእልፍ ታጋዮቹ ፀሎት ይደረግ"ብሎ መጠየቅ ሲገባ፦" ለምን ለዘጠኝ ሰዎች ብቻ ፀሎት ይደረጋል?" ማለት፤ ምን ማለት ነው? ወትሮስ፣ ደርግ መቶ ይገድል ነበር፤ እኛኮ ስልሳ ብቻ ነው "ብሎ የሚያስብ ጭንቅላት ስራቱ እንዴት ነው?ይህን ነገር ዛሬ ለማንሳት ያስገደደኝ፣ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በረሀብ በአስደንጋጭ ሁኔታ እንደ ንጋት ጤዛ እየረገፉ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ ገዥዎቻችን እየተናገሩት ያለው ነገርና እየሰጡት ያለው መልስ አንዳንድ ወዳጆቼን እንደ አዲስ ሲያስገርማቸው ዐይቼ ነው።እናም መፅሐፉ፦" ከፀሀይ በታች አዲስ ነገር የለም" እንደሚል፤እኔም፦"ጭካኔ ለኢህአዴግ አዲስ አይደለም-ተፈጥሮው እንጂ" ልላቸው ፈለግኩ።

የድርጅቱን ታሪካዊ አመጣጥ የሚያውቁት የገዛ አባላቱ እንደጀብዱ የሚናገሩትን አስተውለነው ከሆነ፡ **"ኢህአዴግ ማነው?"** የሚለውን በመጠኑ ያሳየናል። ብዙዎቻችን እንደምናውቀው፤ የዛሬዎቹ ገዥዎቻችን በገዛ ወዳጆቻቸውና ባልንጀሮቻቸው ደም ላይ ተሸጋግረው ነው እዚህ የደረሱት፡፡ለነሱ ስለ ሰብዓዊነት መንገር ጉንጭን ከማልፋት የዘለለ ትርፍ የለውም።ለነሱ የሰው ልጅ ህይወት ዋጋ፤ እንደቁንጫ ነፍስ ነው።

እንግዲህ ዛሬ በረሀብም ይሁን በጥይት "ይኸን ያህል ሰው ሞተ" ሲባል፦ "ተጋኗል የሞተው ይህን ያህል ብቻ ነው" የሚለው ጩኸት የዚሁ ቅጥያ መሆኑ ነው- የባህሪያዊው ወደር የለሹ ጭካኔ። በእርግጥም ዛሬ በአንድ ክልል ብቻ በየቀኑ በአማካይ 400 ህፃናት በምግብ እጦት እየሞቱ እንደሚገኙ በዓለማቀፍ ሚዲያዎችና በግብረ-ሰናይ ድርጅቶች እየተመሰከረ ባለበት ሰዓት፤ገዥዎቻችን፦"ችግሩ ከቁጥጥራችን አልወጣም"የሚሉን ሰውነት፣ በነሱ ጠባብ ጭንቅላት- ሚዛን ሊያነሣ ባለመቻሉ ነው።14 ሚሊየን ወገኖች ለከፋ ረሀብና ድህነት መጋለጣቸው ፀሀይ የመታው ሀቅ በሆነበት ሰዓት፤ገዥዎቻችን የኦሎምፒክ ሪከርድ እንደሰበረ አትሌት ደረታቸውን ነፍተውና አፋቸውን ሞልተው፦"ረሀብ በኢትዮጵያ የለም" የሚሉን፤ የሰው ልጆች ውድ ህይወት፤ ለነሱ ምንም ትርጉም ስለማይሰጣቸው ነው።አባትና እናቶቻችን፦"በዘመናችን እንዲህ አይነት ችጋርና ረሀብ አይተን አናውቅም" ብለው በረሀብ አንጀት ምህላ በያዙበት ጊዜ፤ ገዥዎቻችን ነፍሳት የሚድኑበትን መንገድ በመዘየድ ፋንታ- ቁጥር መደመርና መቀነስ ላይ ተጠምደው የከረሙት፤ የተቀመጡበት ወንበር ራስን አዋርዶ ህዝብን ማዳንንና ማክበርን የሚጠይቅ አደራ ያለበት መሆኑን፡በጭራሽ ስለማያውቁትነው።በእርግጥ፤ዓለማቀፉ-ህብረተሰብ፦"የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተስፋ እያስቆረጠን ነው" በሚልበት በአሁኑ ወቅት፤ ገዥዎቻችን ስለ ድህነት ቅነሳ የሚነግሩን፤ ለነሱ ድህነት ቅነሳ ማለት- ህዝብን በረሀብ መቀነስ ማለት ይሆን ወይ አያሰኝም ትላላችሁ? እኒያ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ እንደተናገሩት፤ ረሀቡ ከቁጥጥራችን ወጥቷል እንዲባል ስንት ሰው መሞት አለበት? 500 ሽህ?1 ሚሊየን? ወይስ 5 ሚሊየን?

ረሀቡና ችጋሩ በአገራችን ከተከሰተ ረዥም ጊዜ ቢያስቆጥርም፤ገዥው መንግስት ችግሩን በማመን ህይወት ወደማዳን ተግባር መረባረብ ሲገባው(ፖለቲካዊ ኪሳራውን ለመጠበቅ ሲል) እውነታውን ደብቆ በመቆየቱ፤ አደጋው ዛሬ ሊደበቅ የማይችልበት ደረጃ ደርሶ የዓለማችንን ትኩረት ስቧል።አሁን አሁን ቢ.ቢ.ሲ፣ ሲ.ኤን.ኤን፣ ሎስ አንጀለስ ታይምስ፣ ሬውተርስ፣ አሶሲየትድ ፕሬስ፣ አጃንስ ፍራንስ ፕሬስ፣ ዩ.ኤስ ቱዴይ፣ ኤሪንና ሌሎች ዓለማቀፍ ሚዲያዎች የዘገባቸው መሟሻ የኛው አገር ረሀብና ችጋር ሆኗል። ዩኒሴፍ፣ ሴቭ ዘ ችልድረን ዩኬ፣ ዶክተርስ ዊዚ አውት ቦርደርስ እና ሌሎች ተሰሚነት ያላቸው ተቋማትም መግለጫዎቻቸውን በኢትዮጵያ ረሀብ ጀምረው በኢትዮጵያ ረሀብ መቋጨት ከያዙ በጣም ሰንበትበት አሉ። እንደነዚህ ተቋማት ሪፖርት ከሆነ፦ **የተከሰተው ረሀብና ችጋር እየተባባሰ እንጂ እየቀነሰ አልመጣም።በአራት ክልሎች ብቻ ተወስኖ የነበረው ረሀብ፤ በአሁኑ ጊዜ አድማሱን በማስፋት በበርካታ ክልሎች በአስፈሪ ሁኔታ ተንሰራፍቷል፤ ሰዎች በብዛት መሞት ጀምረዋል፤ምንም የሚታይ ተስፋ ስለሌለ በቀጣዮቹም ወራት እየከፋ ይሄዳል።**

እነ "ኩት አትበሉን የሹም ዶሮዎች" ግን፤ በስድብ ከጥፋት የዳነ አገር ያለ ይመስል፤ "አዎ ተርበናል፣ ድረሱልን!" በማለት ፋንታ፤ በዓለማቀፍ ተቋማቱ ላይ የስድብ አፋቸውን አላቀዋል። እነሱን ያመማቸው የወገን መርገፍ ሳይሆን፤ በኢትዮጵያ ረሀብ ገብቷል የሚለው ዜና መነገሩ ነው-የውሸት ዕድገት ዲስኩራቸውን ፉርሽ አደረገባቸዋ።

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

ወገኖቻችን በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የሚልሱትና የሚቀምሱት አጥተው በረሀብ እየረገፉ ነው።ይህንን አስደንጋጭ የወገን እልቂት የፓለቲካ መነገጃ ማድረግ በማናቸውም የሞራል መለኪያ ተቀባይነት የሌለው ከባድ ወንጀልና ህዝባዊ ክህደት ነው።ይህን የወገን ሞት ደጋግመን ምናወሳው፤ የገዥዎቻችን ጭካኔና ግፍ ሊሸፋፈን በማይችል መልኩ መገለጥና መጋለጥ ስላለበት ነው።ከዚህም ባሻገር ይህን ዕውነታ በአግባቡ መረዳት፤ አገርና ወገን ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ የአገራችንን ዋነኛ ችግርና የችግር መንስዔ፤ እንዲሁም ይህን ችግር ስር ነቀል በሆነ መንገድ ለማስወገድ መወሰድ ባለበት የተባበረና የተሳሰረ እርምጃ ዙሪያ አንድ ዓይነት አቋም እንድንይዝ ያስችለናል የሚል እምነት አለን። ስለዚህም፤ ሁላችንም በያለንበት እንምከር፣ እንነጋገር፣ **"የአገሬንና የህዝቤን ችግር ለመፍታት ምን ማድረግ አለብኝ?"ብለን እያንዳንዳችንራሳችንን እንጠይቅ።**

**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**

አሳርና መከራ ውስጥ የገባው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ከጨካኞች ጥርስ እንዲላቀቅ ምን እናድርግ? "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል፤ አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫዎቻ ይሆናል" እያልን ትንታ ያለውን ትዝታ በማጣጣም ጊዜ የሚያመጣውን እየጠበቅን በዝምታ እንቀጥል? ወይስ እየወደቀችና እየተናጠች ያለችው አገራችን ጨርሳ በህዝባዊ ቀውስ ሳትፈራርስ በጋራ እንነሳ? አባት ምን ይሰማዎታል? እናት ምን ይሰማዎታል? ወንድሞች ምን ይሰማችሁዋል? እህቶችስ ምን ይሰማችሁዋል? ከዚህ ጭካኔ ለመገላገልሽ፣ ከዚህ ጨካኝና ጨቋኝ አገዛዝ ለመላቀቅ ምን እናድርግ?